

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር 19

ሠመራ ጥር ፳፯ቀን፲፱፻፺፭ ዓ.ም

በብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ምክርቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 19

Samara 7th, 2002

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የም/ቤት አባላት የመረጣቸው ህዝብ አመኔታ ባጣባቸው ጊዜ ስለሚወሰደው እርምጃ የወጣ አዋጅ
---------- ገጽ ፭

አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የም/ቤት አባላት በመረጣቸው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ስለሚወሰደው እርምጃ፣ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፭፣

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ህገ-መንግስት በአንቀጽ ፶፪ ስር ማንኛውም ኃላፊና የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን እና በማንኛውም የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ም/ቤት አባል በመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ የሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፣

በዚህም መሰረት ይህ መሰረታዊ የተጠያቂነት ሕገ-መንግስታዊ መርህ ስራ ላይ እንዲውል የሚያስችል ህግ አስፈላጊና ወቅታዊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ የ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ህገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯/ፎ/ሀ መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ አንድ

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የም/ቤት አባላት የመረጣቸው ህዝብ አመኔታ ባጣባቸው ጊዜ ስለሚወሰደው እርምጃ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፩ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ክፍል ሁለት

አንቀጽ ሁለት

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦-

፩. " ተመራጭ" ማለት በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ አፈጻጸም ህግ መሰረት አንድ አካባቢን ለመወከል የተመረጠና በምርጫ ቦርድ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የም/ቤት አባል ነው።

፪. "የምርጫ አካባቢ " ማለት በምርጫ ህግ መሰረት የተወሰነ የህዝብ ብዛት የሚያካትት አካባቢና ልዩ የምርጫ አካባቢ ማለት ነው።

፫. "መራጭ " ማለት በምርጫ ህግ መሰረት እድሜው /ዋ/ አሰራ ስምንት ዓመት የሞላው /ላት/እና በምርጫ አካባቢው ከሁለት አመት በላይ የተቀመጠ /ች/ ግለሰብ ነው።

፬. "ወረዳ " ማለት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ ---------- መሰረት የተደራጀ ከቀበሌ በላይና ከክልል መስተዳድር በታች የሆነ ደረጃ /እርከን/ ነው።

፭. "ቀበሌ " ማለት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ ---------- መሰረት የተደራጀ ዝቅተኛ /ታችኛው/ የመስተዳድር ደረጃ /እርከን/ ነው።

፮. "ምክር ቤት " ወይም "የምክር ቤት አባላት " ማለት እንደቅደም ተከተላቸው በአፋር ብሔራዊ ክልል ተቋቁመው የሚገኙ የክልል፣ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች ወይም የም/ቤት አባላት ማለት ነው።

ክፍል ሶስት

መብቶችና ግዴታዎች

አንቀጽ ሶስት

መሰረታዊ መብቶች፣

፩. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግዛት ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ህግ በሚፈቅደው መሰረት

በአፋር ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የሚወከል ተመራጭ የመምረጥ መብተ አለው።

፪. በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ከሌሎች ጋር በመሆን መርጦ የወከለውን ተወካይ

በፈለገው ጊዜ መመርመር፣ መገምገም፣ መመዘን ይችላል።

፫. በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚኖር ማንኛውም ዜጋ መርጦ ለወከለው ተወካይ ሲሰጠው የቆየውን ድጋፍ

የመሰረዝ የማቋረጥ፣ ወይም የመቀጠል መብተ አለው።

፬. ማንኛውም የህዝብ ተመራጭ /የምክር ቤት አባል/ በመራጮቹ የሚቀርብለትን ምስጋና፣

ተግሳፅ/እርማት/ግምገማ ወይም ሂስ በግልፅና በአደባባይ የማሰራጨት፣ የመቃወምና የመንቀፍ መብት

አለው።

<u>አንቀጽ አራት</u>

<u>የህዝብ አመኔታ የሚለካበት አግባብ</u>

አንድ የህዝብ ተወካይ /ተመራጭ/ የህዝብ አመኔታ የለውም ሊባል የሚችለው፦

፩. ተወካይ በተወከለበት የምርጫ አካባቢ የሚገኙት መራጮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ምርጫ

ባወጣው ደንብ መሰረት እንዲወርድላቸው ለምርጫ ቦርድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣

፪. ከዚህ በላይ በንዑስ ቁጥር ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተወካዩ በተወከለበት የምርጫ አካባቢ

ከሚገኙ መራጮች ማመልከቻ ሲቀርብና ምርጫ ቦርድ ባወጣው ደንብ መሰረት ም/ቤቱ በ፪/፫ኛ

ድምጽ ውሳኔ ያስተላለፈ እንደሆነ፣ ወይም ደግሞ የክልሉ ምክር ቤት የህዝብ ውክልና ኃላፊነት

ያጓደለ ተወካይ ጉዳዩ በ፪/፫ኛ ድምጽ ወስኖ ተወካዩ በተወከለበት የምርጫ አካባቢ ለሚገኙ

መራጮች አቅርቦ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምርጫ ቦርድ ባወጣው ደንብ መሰረት ተወካዩ

እንዲወርድላቸው ሲጠይቁ የሚፈጸም ይሆናል።

፫. የልዩ ምርጫ አካባቢ ተወካይ የሚመለከት ከሆነ በምርጫ ቦርድ ህግ መሰረት ተወካዩን

የመረጠው ህዝብ በተወካዩ ላይ አመኔታ ማጣቱ ሲረጋገጥ።

፱. በየደረጃው ያለው ምክር ቤት ተወካዩ ባሣየው የስነ-ምግባር ጉድለት የወከለውን ህዝብ በብቃት

ሊወክለው አይችልም ብሎ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የወሰነ እንደሆነ ነው።

<u>አንቀጽ አምስት፣</u>

<u>የስነ-ምግባር መመዘኛዎች</u>

አንድ የምክር ቤት አባል በስነ-ምግባር ጉዳለት እርምጃ ሊወሰድበት የሚችለው ቀጥለው ከተዘረዘሩት የስነ-ምግባር ጉድለቶች ቢያንስ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ፈጽሞ ሲገኝ ነው።

፩.ጉቦ መቀበል፣

፪. በወገን/በዘመድ/በጐሳ፣ በአካባቢያዉነት ሲሰራ፣

፫. የህዝብና የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለግል ጥቅም ሲያውል፣

፬. በሀይማኖት፣ በዘር፣በአካባቢያዊነት፣ በጐሳ ሆነ ብሎ ህዝብ ሲከፋፍል

፭. በህብረተሰቡ አስነዋሪ ተብለው የሚታወቁ ስነ-ምግባሮችን ፈጽሞ ሲገኝ፣

፮. ሆነ ብሎ ለመንግስትና ለህዝብ የሚጐዱ ትላልቅ ወንጀሎችን ሲፈፅም፣

<u>አንቀጽ ስድስት</u>

<u>ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፣</u>

፩. ምክር ቤቱ በሚያቋቁመው ኮሚቴ አማካየነት በስነ-ምግባር ብልሹነት የተከሰሰ ተወካይ ጉዳዩ

ይጣራል።

፪. የምክር ቤቱ አጣሪ ኮሚቴ የሰጠው ውሳኔ መሰረት በማድረግ ከተወያየ በኃላ ይወስናል።

፫. ምክር ቤቱ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተወካዩ ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስዱ

ይችላል።

ሀ/ ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ ማስጠንቀቂያ፣ ተግሣጽ ወይም ሂስ መስጠት፣

ለ/ ለተወሰነ ጊዜ ከምክር ቤቱ ማገድ፣

ሐ/ የስነ-ምግባር ብልሹነት አለው ተብሎ የታመነበት አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) /ሀ/ እና /ለ/

የተደነገጉትን ቅጣቶች ከተቀበለ በኃላ የስነ-ምግባር ብልሹነቱን የሚቀጥልበት ከሆነ በሁለት ሶስተኛው

የምክር ቤቱ ድምጽ ከአባልነቱ ይሰረዛል፡-

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫/ "ሀ" እስከ "ሐ" የተመለከቱት ቅጣቶች ቅደም ተከተላቸውን ሣይጠብቁ

ሊፈፀሙ ይችላሉ።

<u>አንቀጽ ሰባት</u>

የምክር ቤት አባልነት መሰረዝ የሚኖረው ውጤት

፩. አንድ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምክር ቤት አባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ አራት /፬/ እና

ስድስት /፮/ መሰረት የውክልና ወንበሩን ሲያጣ ከምርጫ ቦርድ የተሰጠው የተወካይነት ምስክር

ወረቀት ህጋዊነት ያበቃል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት

ምክር ቤት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የተጓደለውን የተወካይነት ወንበር በማሟያ ምርጫ እንዲሟላ

ሊያደርግ ይችላል።

<u>አንቀጽ ስምንት</u>

<u>አዋጅ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ_____ ፲፱፻፺፭ _____ ዓ.ም

ኢስማኢል አሊ ሲሮ

የአፋር ብ/ክ/መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር